ወጥመዱ ለማን ነው?

ናዚዎች ፖላንድን በወረሩ ጊዜ የሆነውን ከአንድ መጽሐፍ እንዲህ አንብቤ ነበር። መጀመርያ ናዚዎች እኛ ሠፈር መጥተው ሰዎችን ይዘው ሲሄዱ ደነገጥን። በኋላ ስናጣራ ናዚዎች አይሁዶችን እየወሰዱ መሆኑን ሰማን። እኛ አይሁድ ስላልሆንን ፈጣሪን አመስግነን ዝም አልን። በሌላ ጊዜ ደግሞ መጥተው እንዲሁ ሰዎችን ወሰዱ። ለካስ የወሰዷቸው ሩሲያዎቹን ነው። እኛ ሩስኪ ስላልሆንን ደስ ብሎን ከረምን። በሌላ ጊዜ መጥተውም ሌሎች ሰዎችን ወሰዱ። ስንሰማ የሌላ ሀገር ዜጎችን እየለቀሙ ነው። እኛ ሆላንዳውያን ነንና በሰላም መኖር ቀጠልን። እንደዚሁ ሌላ ጊዜ መጥተው በሠፈራችን የቀሩትን ለቃቀሙ። አሁን ደግሞ ካቶሊክ የሆኑትን ነበር የወሰዱት። ሲልልን ካቶሊክ አይደለንም። ግን ሠፈርተኛው ሁሉ አለቀ።

በመጨረሻ አንድ ቀን መጡና እኛን ወሰዱ። በአካባቢያችን ማንም አልቀረም። ብን ጮኽ እንኳን የሚሰማን፣ ስለኛም የሚጮኽ አላገኘንም። ምክንያቱም ሁሉም ከኛ በፊት ሄዷልና። የመጀመርያዎቹ ሰዎች ሲወሰዱ እኛ ጮኸን ቢሆን ኖሮ ዛሬ እኛ አንሄድም ነበር። አለዚያም ደግሞ የሚጮኽልን አናጣም ነበር። እኛ ግን የሌሎችን ችግርና መከራ የሌሎች ብቻ አደረግነው። ስለዚህ እጣ ፈንታቸው በከፋ ሁኔታ ደረሰን።

ጣልያን ኢትዮጵያን በ1928 ዓም ስትወርር ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በሊግ ኦፍ ኔሽንስ ስብሰባ ላይ ተናግረው ነበር። ያኔ ግን ከተወሰኑ ሀገሮች በቀር ማንም አልተቀበላቸውም። የኢትዮጵያ መጠቃት ዋናዎቹን ኃያላን ሀገሮች አልተሰማቸውም ነበር። አምስት ዓመት ሳይሞላ ግን ጣልያን ጀርመንን ደግፋ እንግሊዝና ፈረንሳይን ቁም ስቅላቸውን ማሳየት ጀመረች። ያን ጊዜ መጠቃት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ገባቸው። ፋሺዝምና ናዚዝም ፈረንሳይንና እንግሊዝን ሳያፈራርስ ማይጨው ላይ እንዲቆም ማድረግ ይቻል ነበር። ግን ማንም ያቺን የማይጨው ጥቃት የዓለም ጥቃት አድርጎ የወሰዳት አልነበረም።

እኔ የምነካው የት ጋ ስነካ ነው? እግሬን? እጄን? ሆዴን? ጀርባዬን? ቤቴን? ግቢዬን? መብቴን? ጥቅሜን? ሀብቴን? ንብረቴን?

እነዚህ ሁሉ የእኔ መነካት መጨረሻዎች እንጂ መጀመርያዎች አይደሉም። እኔ የምነካው እዚያ ማዶ ያለው፣ ያ የማላውቀው ሰው ሲነካ፣ ሲደፈር፣ ነው። እኔ የምራበው እዚያ ማዶ ያለው ሰው መራብ ሲጀምር ነው። እኔ የምሞተው እዚያ ጋ ያለው ሰው መሞት ሲጀምር ነው። እዚያ ጋ ነኝ እኔ። ከዚያ ነው እኔነት የሚጀምረው። የምከራ

ከረው ለሌላው አይደለም፤ ለራሴ ነው። ላንተ ስታገል፣ ላንተ አይደለም የምታገለው ለእኔ ነው። ይህንን ችግር አንተ ጋ ካላቆምነው፣ አይቀርም እኔ ጋር ይመጣል።

ሰውዬው ባለ መማሩ ይቆጭ ስለነበር አሜሪካን ሀገር ሄዶ እኔ ነኝ ያለ ትምህርት ተምሮ መጣ። ሲመጣ ታድያ ይዞት ያልመጣው ዕቃ አልነበረውም። ማደግ፣ መለወጥ፣ መዘመን፣ መሠልጠን አለብኝ ብሎ ኑሮ የሚያቀላጥፍ፣ ችግር የሚቀርፍ፣ ሥራ የሚያ ቃልል ቴክኖሎጂ ሰብስቦ መጣ። በኤሌክትሪክ የሚከፈት በር፤ በፀሐይ ሙቀት የሚ ሠራ ማብሰያ፤ ሲናገሩት የሚከፈት ቴሌቭዥን፣ ሲያዙት የሚነጠፍ አልጋ። በዲጂታል ዕቃ የሚያጥብ መሣርያ፤ ምን ያላመጣው አለ።

አዲሱ ቤቱ ገባ። ዘበኛውን ቀጠረ። የቤት ሠራተኛዋን ቀጠረ። ኑሮ ጀመረ።

አንድ ቀን ዘበኛው የበሩ መክፈቻ ኮድ ጠፋውና በድንጋጤ ሲሞካከር መክፈቻውን አበላ ሸው። የሚመጣውን አደጋ ስላወቀ ቀስ ብሎ ከቤት ጠፋ። የቤት ሠራተኛዋም መሣር ያው በተበላሸ ቁጥር የመንደሩን ጎርጓሪ እየጠራች ስታስጠጋግን ከርማ ከአቅሟ በላይ ሲሆን ጥላ ሄደች።

ሰውዬው ሌሎች ሠራተኞች አምጥቶ ሊያሳያቸው ማዕድ ቤት ሲገባ መሣርያው ሁሉ በፕላስተርና በገመድ ተጠጋግኖ አገኘው። አበደ፤ ጮኸ። ውጭ ሲወጣ ደግሞ በሩ እንደ ነገሩ በእጅ ነበር የተዘጋው። የሩቅ መቆጣጠርያው አይሠራም። እየዞረ የቤቱን ዕቃ ሲያይ ግማሹ ተበላሽቷል፤ ግማሹ ተጎርጉሯል። አብዶ አብዶ ሲጨርስ ሠሪ ለማምጣት ሄደ። ግን ያንን ቴክኖሎጂ የሚሠራ ሰው በሀገር አላገኘም። እንደገና ከውጭ ማምጣት ሊኖርበት ነው። ነገር ግን የሚያስገባቸውን ሠራተኞች ሲያስብ እስከ መቼ እያስመጣ ሊያስጠግን እንደሚችል ገመተና ሰለቸው።

ተማርሮ ጓደኛው ጋር ሄደ። እያማረረ ነገረው። ጓደኛውም ሰማው። እንዲህም አለው። «ወዳጄ ብቻህን ልታድግ አትችልም። አንተ ያንተን መማርና መለወጥ ብቻ ነው ያየ ህው። ሀገር ካልተማረ ፣ ሀገር ካልተለወጠ ብቻህን ልትለወጥ አትችልም። ምግብ የምት ሠራልህ፣ ቤት የምታጸዳልህ፣ መኪናህን የሚሠራልህ፣ ግቢህን የሚጠብቅልህ፣ ምግብ ቤት የሚያስተናግድህ፣ ቢሮ የሚላላክህ፣ ልብስህን የሚያጥብልህ፣ እነዚህ ሁሉ አብረው ካልተለወጡ ብቻህን ምን ልትሠራ ትችላለህ? አንተ የምትኖረው ከእነርሱ ጋር ነውኮ። ደስተኛ ሆነህ መኖር ከፈለግህ እነርሱንም ለውጣቸው። የእነርሱ አለመለወጥና አለመማር ካልገደደህ፣ ችግራቸውን ችግርህ፣ ኋላ ቀርነታቸውንም ኋላ ቀርነትህ አድርገህ ካላየኸው ዕዳው ላንተ ጭምር ነው የሚተርፍህ።

አንተ ብቻህን ስለ ጤና አስበህ የትም አትደርስም። አካባቢህ በሙሉ ካላሰበ በቀር። አንተ ስንቱን ታጸዳለህ? አንተ ቤት የምትመጣው ዝንብ ካንተ ግቢ ብቻ ነው እንዴ የምትነሣው? አየሩ ላይ የሚረጨውን ቫይረስ አንተ ብቻህን ትከላከለዋለህ። አንተ ስትስል አፍህን ትሸፍን ይሆናል፤ ሌላውም እንዳንተ እንዲያደርግ ካላስተማርከው ግን ከመታመም አትድንም። ጎረቤትህ ቢያንስ አንተ የደረስክበት ለመድረስ የሚጓዝ ካልሆነኮ የርሱም ዕዳ ይመጣብሃል። አንተ በዘመናዊ መኪና ብትሄድ ምን ዋጋ አለው? በመንገዱ አንተ ብቻ ነህ እንዴ የምትሄደው? መንገድ ሠሪው አብሮ ተለውጦ ለዘመናዊ መኪና ዘመናዊ መንገድ ካልሠራ ምን ልታደርግ ትችላለህ? አብሮህ የሚነዳው፣ ባለ መኪናው፣ ሾፌሩ፣ ረዳቱ፣ እግረኛው አብሮ ካልተለወጠ አንተ ብቻህን የት ትደርሳለህ?

አሁንም ብቻህን ለመለወጥና ለማደግ ካሰብህ የትም አትደርስም። የዚያኛው ማደግና መለወጥ ላንተው ለራስህ ነው የሚጠቅምህ። የዚያኛው መዘመንና መሠልጠን ላንተው ነው የሚጠቅምህ። የዝያኛው መማርና ማወቅ ላንተው ነው የሚጠቅመው።

አንተ ብቻህን ሀብታም ሆንክ እንበል። ብቻህን ዲታ ሆንክ። ሌላው ደኸየ። የሚበላው አጣ። አንተ ግን ተተኮስክ። ታድያ እንዴት መኖር ትችላለህ? ድኽነት ወንጀልን ያበረ ክታል። ሰው ሲመርረው የሞራል ሕግጋትን ይጥሳል። ገድሎ፣ ዘርፎ፣ ወርሮ አታልሎ መብላትን መመሪያው ያደርጋል። ታድያ አንተ ያን ጊዜ ሀብትህን ምን ታደርገዋለህ? ወንጀለኛው ከበዛ የት ትኖራለህ? የት ትዝናናለህ? የት ትሠራለህ? በኋላ ደኅንነትህን ለመጠበቅ የምታወጣውን ገንዘብ አካባቢህን ለመለወጥ ቀድመህ ብታወጣው ኖሮ አንተም ወገንህም በሰላም ትኖሩ ነበር።

ወዳጄ አንተ ሀብታም ሆነህ በሰላም ለመኖር ከፈለግህ ያኛውም እንዳቅሙ ሀብታም እንዲሆን እርዳው። ለርሱ ስትል ብቻ አይደለም፤ ለራስህ ስትል። የሌላው ነገር የማይ ገድህ ከሆነ፣ የራስህም ነገር አይገድህም ማለት ነው። እሳቱ ከመንደሩ የመጀመሪያውን ቤት ሲነካ ካላጠፋነው የሁላችንንም ቤት አይምርም። እዚያኛው ቤት ሲቃጠል ውኃ ይገፍ የምሮጠው ለሰዎቹ ብዬ ብቻ ሳይሆን ለራሴም ብዬ ነው። የሰዎችን እሳት እያጠ ፋሁ ብቻ ሳይሆን የእኔንም ቤት እየተከላከልኩ ነው።

አለና የሚከተለውን ታሪክ ነገረው።

በአንድ ቤት ውስጥ አይጥ፣ ዶሮ፣ በሬ፣ ዐሳማና በግ ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን የቤቱ ሰዎች የአይጥ ወጥመድ ገዝተው መጡ። አይጥ ወደ ጓዳ ልትገባ ስትል ወጥመዱ ተዘጋ ጅቶ አየችው። ደንግጣ ስትሮጥ መጣችና ለዶሮው ነገረችው። «አለቅን፤ አለቅን። የአይጥ ወጥመድ ቤቱ ውስጥ ተዘርግቷል» አለቺው። ዶሮውም ክንፉን አማታና ከት

ብሎ በመሳቅ፡ «እና ምን ይሁን? አንቺን ይጭነቅሽ እንጂ» አላት። አይጧ ዶሮውን ትታ ወደ በሬው ጋ ሄደች። «ጉድ ነው፣ ጉድ ነው» አለቺው። «ምን ሆንሽ?» አላት። «የአይጥ ወጥመድ ተዘጋጀ። ማለቃችን ነው» አለቺው።

በሬውም «አይዞሽ እንደ ምንም ብለሽ ማለፍ ነው፤ ለእኔ ግን አታስቢ» ብሎ አጽናናት። ምንም ነገር ግን አላደረገም። እርሷም እያዘነች ወደ ዐሳማው ጋ ሄደች። «ከንግዲህ መኖር አንችልም» አለቺው። «ለምን» አለ ዐሳማው። «የአይጥ ወጥመድ ተዘጋጅቷል» «ያሳዝናል። በይ ተጠንቀቂ። ስትንቀዘቀዢ እንዳትያዢ። እኔን ግን ምንም ስለማያ ደርገኝ አታስቢ» አላት። በመጨረሻ ወደ በጉ ዘንድ ሮጠች። «እዚህ ቤት የሆነውን ሰምተሃል?» አለቺው። «ምን ሆነ» አላት በጉ ደንግጦ። «የአይጥ ወጥመድ ተዘጋጀኮ» «እ፣ እኔ ደግሞ ምን መጣ ብዬ። ታድያ ለሌሎች አይጦች ንገሪያቸው እንጂ ለእኔ ምን ያደርግልኛል። እንኳን እኔን አፍንጫዬን አይነካውም» ብሎ ቸብ ቸብ አደረጋት።

አይጥ ከማንም ትብብርና መፍትሔ ስታጣ ጉድጓዷ ገብታ ማሰብ ጀመረች።

በማግሥቱ የአይጡ ወጥመድ ያዘ። ወጥመዱ ሲንቀሳቀስ ያየቺው የቤቱ እማ ወራ ሮጣ ስትመጣ ለካ እባብ ነው የተያዘው። እባቡ መጠጋታን አይቶ ነደፋት። ሴትዮዋ ታመመች። ባለቤታ ወዲያው ወደ ሐኪም ቤት ወሰዳት። ለሴትዮዋ ማሳከሚያ ገንዘብ ያስፈልግ ስለነበር ሰውዬው ዐሳማውን አርዶ ሥጋውን ሸጠው። ምንም አልሆንም ያለው ዐሳማ የመጀመርያው የወጥመዱ ሰለባ ሆነ።

ሴትዮዋ ከሐኪም ቤት ሳይሻላት ወጣች። እቤት ስትደርስ ባለቤታ ለሚስቱ የዶሮ መረቅ ጥሩ ነው ሲባል ጊዜ ዶሮውን አረደው። አንቺን ይጭነቅሽ ያለው አውራ ዶሮው እርሱ ለመጨነቂያም ጊዜ ሳያገኝ ታረደ። ሴትዮዋ ልትድን አልቻለችም። በዚህም ምክንያት ቤተሰቦቿ ቤታ ውስጥ ሊያስታምሟት ተሰበሰቡ። ሰውዬውም እነርሱን ለመመ ገብ ሲል በጉን አረደው። በመጨረሻም ሴትዮዋ ሳትድን ሞተች።

የቀብሩ ዕለት ለተገኙት አልቃሾች መሸኛም በሬው ታረደ።

ወጥመዱን ለአይጧ ብቻ አድርገው ያሰቡት ሁሉም በወጥመዱ ውስጥ ገቡ። ወጥመዱ የኛ ነው ቢሉ ኖሮ ውጤቱ ሌላ ይሆን ነበር። አሁንም ጥያቄው አንድ ነው። ለአይጧ የተዘረጋው ወጥመድ ለማን ነው?

ሐራሬ፣ ዚምባብዌ